**የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣቶች ክንፍ ድርጅት (ኢወክንድ)**

ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባዔውን አጠናቀቀ፡፡

ላለፉት ድፍን 40 ዓመታት ለኢትዮጵያ የታገለውና አሁንም በትግል ያለው የኢሕአፓ ውልድ የሆነው ኢወክንድ በመስከረም 20, 2004 (October 1, 2011) ሁለተኛ ጉባዔውን አጠናቋል፡፡ለኢትዮጵያ ምድር ለሷ ብሎ በሷ ታምኖ ለፍቅር ደም የከፈለላትን ኢህአወሊን ሀውልት ይሆንለት ዘንድ  የተቋቋመው የወጣቶች ድርጅት ኢወክንድ በተለያዩ ዘመናዊ መገናኛና በአካል እና በውክልና በመገናኘት ሰፊና ጠለቅ ያለ ውይይት አካኢዷል።

በዋናነት የታላላቅ ወንድም እህቶቹን፣አባት እናቶቹን ክብር መስዋዕትነት ክብር ከመስጠት ባሻገር ዓፅመ ርስታችን የሆነችውን ኢትዮጵያ ደምስሯ ላይ የተተከለውን የወያኔ ሥርዓት ለማፍረ እና በእኩልነት ላይ የተመሰረተች አንድነቷ የተጠበቀ ኢትዮጵያን ዝንተ አለማዊ ለማድረግ ትግሉን መሠረት ያደረገው ኢወክንድ የተጨባጭ ሁኔታውን ገምግሞ ያለፈ ዓመቱን ጠንካራና ደካማ ጎን አውጥቶና አውርዶ ለቀጣዩ ዓመት ትግሉን በሀላፊነት የሚመሩ አመራሮችን መረጠ ጉባዔውን አጠናቋል፡፡

የኢሕአፓ ወጣቶች ከኛ በፊት የነበሩ ለሀገር ቀናኢ ሆነው የከፈሉትን መስዋትነት ፈለግ ተከትለን ፅናታቸውን ፀንተን፣ሀገር ወዳድነታቸው ወደን የገባን ወጣቶች ነንና የኢሕአፓን ታሪክ አጉዳፊዎችን እየተቋቋምን ለክብርት ኢትዮጵያ ክብር መስዋትነት ለመክፈል በኢወክንድ መሰለፋችንን ስንገልፅ የኢትዮጵያ ወጣት ሆይ! ባሻህ ድርጅት ተሰለፍ፣ተደራጅ፣ግን ለእመ ኢትዮጵያ እናብር ጥሪውን  በማስተላለፍ የጉባዔውን መጠናቀቅ ያብስራል።

በኢትዮጵያ ጉዳይ አንቀልድ!

ኢወክንድ